# <u>የትውልዱ ትውስታዎች</u>

## በአቶ አሊ ሁሴን ስለቀረበው ፊልም መለስተኛ አስተያየት!

ከዘነበ በቀለ

ይህ በአሮን ፍሎሬሰኮ የተቀናበረው የአቶ አሊ ሰኢድንና የሌሎች ኢትዮጵያውያን የህይወት መከራ የሚገልፀውን ፊልም በስቶክሆልም ከተማ በሮግስቬግ አዳራሽ ተገኝቼ ተመለከትኩት። እንደ አንድ ሀገሩን እንደሚወድ ኢትዮጵያዊ አለቀስኩ። እንደ ጥበብ ሰውነቴም ተዝናናሁ፤ ኮራሁ። ይህ አይነቱ ጭካኔ ከሰው ልጆች የሚጠበቅ ነው ብዬ እራሴን ጠየቅሁ። እራሴን በራሴም ረገምኩ። የዚሁ ትውልድ አካል ነኝና። በእርግጥ ይህን የመሰለውን ግፍና በደል ወገን በወገኑ ላይ ይፈፅማል? ከምን አይነቱ የአስተሳሰብ እርከን ላይ ነው ያለነው? ይህን የሚያደርጉ ሰዎች እውን! ሰውነታችን ዕድገቱን ፈፅሞ በተሟላ ሁኔታ ላይ ነው ብለው ያምኑ ይሆን?

አቶ አሊ የራሱን ገጠመኝና የሚቀርቡትን ጓዶቹን ታሪክ አቀረበው እንጂ! በተመሳሳይ ሁኔታ በሌሎች ስፍራዎች በሺዎች የሚቆጠሩ የተጠቁ ኢትዮጵያውያንም እንደማይጠፉ አመንኩ። እኔ ትል እንኳ ገድዬ አላውቅም የሚለው ኮሎኔል መንግስቱ ይህን ፊልም ሲያይ ምን ይሰማው ይሆን? እንዴት ከዚያ ሩህሩህ ህዝብ ማህፀን እንደነዚህ ያሉ ጭራቆች ሊፈሩ ቻሉ? ይህንን የመሳሰሉ ጥያቄዎች በጭንቅላቴ ውስጥ ሳንገዋልል ቆየሁ። የሰው ልጅ በቀል አዝሎ ይጓዝ ቢባል የድህነት ህይወት ያሳለፈው ሁሉ በቀልተኛ መሆን አይገባው ይሆን? ሆኖም ግን ድሃ "በቀል" አያውቅም። ምናልባት የድሃ አምሮታም፤ ላምሮቱ የተገዛ አይጠፋ ይሆናል። መንግስቱ ሀይለማርያም ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ቤት አደገ የሚባልለት። መለስ ዜናዊ የባንዳ ፊትአውራሪ ልጅ ነው የሚባልለት። እነዚህ ሁለት ፋሽስቶች መነሻቸውን ከብሄረተኝነት ስሜት ላይ ማድረጋቸው፡ በህዝብ ስቃይ የሚደሰቱ መሆናቸውን ማሳየታቸው ላያስደንቅ ይችል ይሆናል። ከነሱ በፊት የነበሩት እነ ሂትለር ብዙ ቆሻሻ ታሪክ ትተው አልፈዋልና። የዚህ አይነት ስሜት የሚሰርፅባቸው ግለሰቦች ሁልጊዜም የበታችነት ስሜት የሚጠናወታቸው ናቸው። ምናልባትም ኮሎኔል መንግስቱ ባሳደጉት ደጃዝማች የተነሳ፡ መለስ ዜናዊ ደግሞ የባንዳ ልጅ መባሉ የበታችነት ስሜት ስለፈጠረበት፤ ሁለቱም ለበቀል ተሰልፈው ይሆናል።

አቶ አሊ በፊልሙ ውስጥ በደንብ ገልፆታል ምንጊዜም ደሃ ለህዝብ አዘኝ መሆኑን። በጎ አሳቢ መሆኑን። ባለራዕይ መሆኑን። ባለተስፋ መሆኑን። ተፈጥሮ በሱ ብትጨክን እንኳ እሱ ግን ርህራሄን ለትውልድ አስተምሮ ሊያሳፍራት ይዘጋጃል እንጂ በሰዎች ላይ በቀል የማይወድ እንደሆነ ያስተምራል ፊልሙ። በጠቅላላው የአቶ አሊን ፊልም ያላያችሁ እንድታዩ! እመክራችሁአለሁ። እውነት አሳቢዎች ማስረጃን ታገኙበታላችሁ። ፊልም ወዳጆች ልቅሶና ሳቅን በአንድ ወቅት እንዴት አድርጎ ማስተናገድ እንደሚቻል ትማሩበታለችሁ። ሀሰተኞችም ፋሽቶችን ደግፎ መቆም ወንጀል እንደሆነ ትረዱበታላችሁ። ይህን የመሰለ እውነተኛ ታሪክ በዚህ መልክ መቅረቡን ከምታደንቁበት መሃል አንዱ ከአቶ አሊ ጋር ከፊልሙ ውጭ የሚደረግ ውይይትን መካፈል ነው።

ቸር ይግጠመን!